# በኢ.ፌ.ድ.ሪ ማዕድን ሚኒስቴር የኦፓል

# ተረፈ ምርት መመሪያ □□□ 278/2013

ሚያዚያ 2007 ዓ.ም

አዲስ አበባ



የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር
መዝገብ ቤት
RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum

# የኦፓል ዉዳቂ/ ተረፈ ምርት መጠን አወሳሰን መመሪያ

## መግቢያ

በባህላዊ መንገድ የሚመረቱ ማዕድናት ግብይት የሚፈፀመው ምርት ከሚመረትበት ቦታ እስከ አዲስ አበባ በሚገኝ የላኪነት ፈቃድ በወሰዱና እደጥበባት በሚሰሩ ፈቃድ ያላቸው አካላትና ፈቃድ በሌላቸው አካላት ጭምር ነው፡፡

በባህላዊ መንገድ ከሚመረቱት ምርቶች አንዱ የሆነው ኦፓል ሲሆን ይህ ማዕድን የሚመረትበት መንገድ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፉ አመራረት ዘዴ ያልተከተለና የምርት ቦታው በገደላማ ቦታ እንደመሆኑ መጠን ለብዙ ብክነት የተዳረገ ነው፡፡ በባህላዊ መንገድ የተመረተው ኦፓል ወደ ገበያ ሲወጣ በዚህ ግብይት ሰንሰለት ተሳታፊ በሆኑ አካላት እጅ ማዕድናቱ ዝውውር ሲደረግ የራሱ የሆነ የምርት ብክነት ወይም የማዕድናቱ ደረጃ መጣት ይፈጠራል፡፡ በተጨማሪ ማዕድናቱን እሴት ለመጨመር ማዕድኑን የመቅረጽ ሥራ ሲሰራበት የማዕድናቱ የብክነት መጠን ይጨምራል፡፡

እንዲሁም የኦፓል ማዕድን በባህርይው ውስን እርጥበት አዘል እንደመሆኑ መጠን በየወቅቱ የክብደት መቀነስ ይገጥማል፡፡

በአገራችን በዚህ ማዕድን ሥራ የሚሰሩ ባለሀብቶች ያለውና በኦፓል ማዕድን እሴት መጨመር ሥራ ለመሳተፍ ማነቆ ሆኖ የታየው ለማዕድን ሥራ እሴት መጨመር የሚባክነው የከበረ ማዕድን ታሳቢ የሚደረግ ግብር አከፋፈል አለመኖር እንደምክንያት ሲቆጠር ቆይቷል፡፡ ይህን ምክንያት በማድረግ በእሴት መጨመርና በግብይት ሰንሰለቱ የሚፈጠሩ ምክንያቶች ግምት ያስገባ የግብር አከፋፈልና ለቁጥጥር እንዲመች የኦፓል ምርት ሂደት ያለውን የብክነት (wastage) መጠን አወሳሰን መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

## የመመሪያው አስፈላጊነት

1. በእያንዳንዱ የግብይት ሰንሰለት ዉስጥ ማለትም ከምርት ማእከል እስከ ኤክስፖርተር ድረስ ያለዉን የምርት መጠን ለመለየት እና የቁጥጥር ስርአት ለመዘርጋት ያስችላል፡፡

2. በግብይት ሰንሰለት ዉስጥ የሚፈጠረዉን አፈርና ከ1ሚሊግራም በታች የሆነዉን ቀለም ያለዉን ማዕድን በመለየት ለሌላ አገልግሎት እንዲዉል ለማድረግ ያስችላል፡፡

3. በትክክል ከተመረተዉ ዉስጥ በዉዳቂ የሚለየዉን ከአካባቢ ብክለት ነፃ በማድረግ ለማስወገድ የሚቻልበትን ስርአት መፍጠር፡፡

4. በዉዳቂ /rejection/ ምክንያት ለሚነሱ የግብር ክፍያ ጥያቄ ለመመለስ እንዲቻል ምን ያህል መጠን እንደሚሆን በመለየት ምላሽ ለመስጠት ያስችላል፡፡ በዚህም ምክንያት ከዚህ ጋር



መዝገብ ቤት RECORD Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Mines and Petroleum

ተያይዘው የሚነሱ ጥያቄዎችና ቅሬታዎች ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት እንደ መሰናክል የሆነውን ለማስተካከል ይረዳል፡፡

5. አመታዊ የማዕድናት ምርት መጠን ለመቆጣጠርና ከዘርፉ የሚገኘዉን ገቢ ለመገመት ያስችላል፡፡

## ዓላማ

ማዕድናት ከምርት ቦታ በግብይት ወቅት እስከ ወደዉጭ እስኪላክ ድረስ ያለዉን የዉዳቂ/ብክነት ወይም ተረፈ ምርት /rejection/ መጠን በእያንዳንዱ ተዋናይ እጅ ወደቂ የሚፈጠርበትን ሁኔታና መንገድ በመለየት ከተገዛዉ ጥቅል ኪሎ ግራም ሊፈጠር የሚችለዉን የዉዳቂ መጠን ለአገልግሎት የማይዉል እና ለሌላ ጥቅም ሊዉል የሚችለዉን በመጠን በመለየት መወሰን እንዲቻል ለማድረግ ነዉ፡፡

## ለዉዳቂ ወይም ተረፈ ምርት /rejection& wastage/መከሰት ምክንያቶች

1. በምርት ወቅት ማዕድን ለማዉጣት በሚጠቀሙበት መቆፈሪያ በሀይል ወይም ያለጥንቃቄ መምታት ማዕድኑ በመጠኑ በጣም ደቃቅ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

2. ማዕድኑ ከተመረተ ሙቀት ወይም ነፋስ ሲያገኘዉ የመሰንጠቅ፡፡

3. ከምርት በኋላ በአግባቡ በጥንቃቄ ለይቶ ለብቻዉ አለማስቀመጥ፡፡

4. በምርት ወቅት ከነሙሉ አፈሩ ማዉጣት እና ለገበያ ማቅረብ ፡፡

5. እሴት በመጨመር ወቅት ቅርፅ ለማስያዝና በላዩ ላይ ያለዉን አፈር ወይም ባእድ ነገር ለማስለቀቅ ሲባል የሚፈጠር ብክነት፡፡

6. በማንንገዝ ወቅት ሊከሰት በሚችል እንቅስቃሴ የሚፈጠር

7. በቆይታ ወቅት የሚፈጠር የክብደት መቀነስ/ በቆይታ የእርጥበት መዉጣት/



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር
መዝገብ ቤት
RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Mines and Petroleum

## በተረፈ ምርት ወይም ወደቂ /rejection & wastage / ላይ ያለዉ ነባራዊ ሁኔታ

ይህ ተረፈ ምርት ዉዳቂ /rejection/ በሁለት አይነት መንገድ ከፋፍሎ መመልከት ለዉሳኔ አሰጣጥ ትልቅ ምልክታ ይሰጣል፡፡ የመጀመሪያዉ በእሴት መጨመር ወቅት የሚፈጠረዉ ተረፈ ምርት አፈርና ድንጋዮች በጣም ደቃቅ የሆኑ በፈሳሽ መልክ የሚወገድ ሲሆን ይሄኛዉ ማንኛዉም የማስጌጥ ስራ ሲሰራ የሚከሰት ሲሆን በዚህ ወቅት እስከ 45% ከሚጠረበዉ ዉስጥ አሴት በሚጨመርበት ወቅት የሚወገድ ነዉ፡፡ በመሆኑም በእሴት መጨመር ወቅት ወደ ተፈለገው ቅርጽ ለማስያዝ ሲባል የሚከሰት ሲሆን ይህም ከአጠቃላይ ክብደት ማለትም ከ1 ኪ.ግ ላይ 3/5 ይቀንሳል፡፡

**የኦፓል ማዕድን የጉድለት መጠን አወሳሰን ስታንዳርድ በምርት አይነትና ደረጃ እንዲሁም በግብይት ወቅት የሚከሰት ዉዳቂ ወይም ተረፈ ምርት /rejection& wastage /**

## ክሪስታል ኦፓል

ክሪስታል ኦፓል በተፈጥሮ ባህሪዉ በቀላሉ እርጥበት ሲያጣ በነፋስ በሙቀት እና በፀሃይ የመሰነጣጠቅ እና ሙሉ ለሙሉ ቀለሙን የማጣት ሁኔታ ሊያጋጥም ይችላል፡፡ይህ የሚፈጠረዉ በገኘዉ በሻጩ ወይም በአምራቹ የጥንቃቄ ጉድለት ሊፈጠር ይችላል፡፡ ይህ ክሪስታል ኦፓል ከተሰነጣጠቀ በኂላ ጥቅም ላይ አይዉልም ማለት አይደለም ይህም ማለት ድንጋይ ለሚሰበስቡ ሰዎች መሸጥ ይቻላል አንዳንዱም ለተለያዩ ነገሮች ማስጌጫነት ይሆናል፡፡ ነገር ግን ለመቅረፅ እና ቅርፅ ማስያዝ አይቻልም ምክኒያቱም ቅርፅ ለማስያዝ ወይም ለመጥረብ ዉሃ ዉስጥ ከገባ የመበታተን የመፈረካከስ እና ቀለሙን የማጣት እድል ያጋጥመዋል፡፡ ስለዚህ ምንም ዋጋ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## አጃራ ኦፓል /gam/

ይሄኛዉ የኦፓል አይነት የሚቀረፅ በቀላሉ የማይሰባበር ወይም የማይሰነጣጠቅ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በትርጽ ማስያዝና ባእድ ነገሮችን ለማስለቀቅ በሚደረግ ወቅት ዉዳቂ ወይም ተረፈ ምርት



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር
መዝገብ ቤት
RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum

/rejection/ ይፈጠራል በተመሳሳይ በክበደቱ ላይ የመቀነስ ሁኔታ አለ ይህም ከ1ኪሎ እስከ 50 ግራም ሊቀንስ ይችላል።

## ሊፈጠር የሚችል ዉዳቂ

ሰንጠረዥ1.1 ላኪዎች በግብይትና ወደ ወጭ ሲልኩ የሚያጋጥም ተረፈምርት

| ደረጃ | የተረፈ ምርት(ውዳቂ) ምክንያት | | | አጠቃላይ ድምር |
|---|---|---|---|---|
| | አፈርና ባእድ ነገር ቅልቅል | መሰባበር መፈረካከስ/መሰነጣጠቅ | በሙቀት ወይም በመትነን | |
| 1ኛ | 50ግራም | 80ግራም | 50ግራም | 180ግራም |
| 2ኛ | 70ግራም | 50ግራም | 30ግራም | 180ግራም |
| 3ኛ | 160ግራም | 60ግራም | 20ግራም | 200ግራም |

ሰንጠረዥ1.2 እሴት በመጨመር ወቅት( ላፒደሪ ) የሚፈጠር ተረፈ ምርት

| ደረጃ | የተረፈ ምርት(ውዳቂ) ምክንያት | | | | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|
| | አፈርና ባእድ ነገር ማስወገድ | መሰባበር መፈረካከስ/ መሰነጣጠቅ | በሙቀት ወይም በመትነን የሚፈጠር ክብደት መቀነስ | ቅርጽ ማስያዝና ማለስለስ | |
| 1ኛ | 50ግራም | 80ግራም | 50ግራም | 350ግራም | 530ግራም |
| 2ኛ | 70ግራም | 50ግራም | 30ግራም | 300ግራም | 480ግራም |
| 3ኛ | 160ግራም | 20ግራም | 20ግራም | 150ግራም | 350ግራም |
| | | | | | |



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር
መዝገብ ቤት
RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum

## የተቀመጠው የዉዳቂ መጠን አወሳሰን ስታንዳርድታሳቢ የተደረገበት ምክንያት

1. የኦፓል ማዕድን በምርት ጊዜና በግብይት ወቅት የመሰባበር የመሰንጠቅ ሁኔታ ስለሚፈጠርበት ወደ ዉጭ ሀገር በኤክስፖርተሮች ሲላክ የግዥ መጠን እና የሚላከዉ መጠን ስለሚቀንስ ይህንን የጉድለት መጠን ምክንያት በ% ለማስቀመጥ ፤

2. በሙቀት በነፋስ እና በፀሀይ ምክንያት የሚፈጠረዉን መሰንጠቅ የኦፓሉን ዋጋ የሚቀንስ በመሆኑ የክሪስታል ኦፓል ዋጋ በዉዳቂ /rejection/ መልክ ሳይሆን በሌላ ዋጋ የሚስተናገድበትን መንገድ ታሳቢ ለማድረግ፣

3. በዉዳቂ /rejection/ ተብሎ የተለየዉ ከ 1ሚ.ግ በታች የሆነዉ ለተለያየ ጥቅሞች የሚዉል በመሆኑ በዉዳቂ ለተቀመጠዉ ዋጋ እንዲወጣለት በማስፈለጉ ምክንያት፣

4. በቅርፅ ማዉጣት ወይም በመጥረብ ጊዜ የሚቀንሰዉን ከግምት በማስገባት በ53%-35% ተቀናሽ ለማዘጋጀት እንዲቻል ታሳቢ በማድረግ እንዲያገለግል፣

## የዉዳቂ ወይም ተረፈ ምርት/rejection/ መጠን አወሳሰን ስታንዳርድ መሰረት ግልጋሎት ላይ የሚዉለዉ ወይም የሚወገድበት አግባብ

1. በቅርፅ ማዉጣት ወይም በማስጌጥ ስራ ላይ የሚፈጠረዉ የመጠን ወይም የኪሎግራም ማነስን በዉሃ ዉስጥ ወይም በሽርፍራፊ መልክ ወደ ደቃቅ ፈሳሽነት የሚለዉጥ በመሆኑ በአወጋገድ ስርአት ላይ የሚገኝ ጠጣር ነገር ባለመኖሩ የሚወገደዉ በዉሃ ወይም በፈሳሽ መልክ ብቻ ይሆናል፡፡ ስለዚህ በቅርፅ ማዉጣት ወይም በማስጌጥ ጊዜ የሚኖረዉ የክብደት መቀነስ ከአፈርና ከባእድ ነገር ጋር የተያያዘ በመሆኑ የተቀነሰዉ የክብደት መጠን በኪ/ግ ከ 1 ኪ.ግ 53%-35% 3/5 ያህል ዉዳቂ ተረፈ ምርት /rejection/ ተብሎ እንዲቀነስ ወይም የተወገደ ተብሎ ይታሰባል፡፡

2. ለኤክስፖርት ወይም ለጌጣጌጥ መስሪያ ተብሎ የተገዛ የኦፓል ድንጋይ የተገዛዉ ወይም ሊገዛ የታሰበዉ በድርድር ላይ ያለ በቅድሚያ በተረፈ ምርት እንዲመዘገብለት ማዕድን ሚኒስቴር ገበያ ልማት ትስስርና ዋጋ ትመና ዳይሬክቶሬት በመቅረብ ማዕድኑን እና ከተገዛበት ወረዳ የመጣዉን ሮያሊቲ ክፍያ የተፈፀመበት ደረሰኝ ማህበራት የሸጡበት ደረሰኝ እንዲሁም አዘዋዋሪ የሸጠበት ደረሰኝ እና ከተፃፈ 5 ቀን ያላለፈው የይለፍ ወረቀት በመያዝ በመምጣት



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር መዝገብ ቤት RECORD Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Mines and Petroleum

ማስመዝገብ ይኖርባቸዋል፡፡ ነገር ግን ይህ ካልሆነ /ካልተመዘገበ / የተረፈ ምርት ምዝገባ እና አቀናነስ አይመለከተዉም፡፡

3. በተራ ቁጥር 2 ያለዉ መረጃ አሟልቶ በጣጣር ማለትም አፈር የሌለዉ እና ከ0.001ግራም በታች የሆነ ለመጥረብ የማይሆን ሆኖ ከተገኘ በተረፈ ምርት ተመዝግቦ በማዕድን ሚኒስቴር ማረጋገጫ መሰረት ለንግድ ሚኒስቴር በማሳወቅ ከተፈቀደ በኂላ ለጌጣጌጥ ስራ ለሚፈልጉ ህጋዊ አካላት ወይም ለዉጭ ሀገር ፈላጊዎች እንዲሸጥ ይደረጋል፡፡

4. ለላኪዎች ወይም ለላፒደሪ ባለፍቃዶች በፌድራል ማዕድን ሚኒስቴር ፍቃድ ወስደዉ በግብይት ወይም በእሴት መጨመር ስራ ላይ ለተሰማሩ ህጋዊ አካላት በትክክል መረጃዎችን ማለትም ደረሰኝ የይለፍ ደብዳቤ ከተገዛበት ወረዳ ማዕድን ቢሮ አስፈላጊ ማረጋገጫ አሟልቶ ለሚገኝ ህጋዊ ላኪ ገዝቶ ያስመዘገበዉ እና ወደዉጭ የላከዉ የምርት መጠን እንደ ማዕድኑ ደረጃ በተቀመጠዉ የዉዳቂ ወይም ተረፈ የምርት መጠን /rejection/ መሰረት በማቀናነስ በእጃቸው የሚገኘዉን በማስቀመጥ በተረፈ ምርት መመሪያ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግና ለመቆጣጠር የሚያስችል መመሪያ ሆኖ ያገለግላል፡፡

- ገገርው ሽያጩን የፈጸመው አዘዋዋሪ የዘመኑን እድሳት ያደሰ መሆኑን በማረጋገጥ ግብ ይት መፈጸም ይኖርበታል፡፡ አዘዋዋሪው የዘመኑን እድሳት ሳይፈጽም ቀርቶ ወይም ከወረዳው በቂ ምክንያት ሳይኖረው ወይም ከህገወጥ የተገዛ እና ህጋዊነት በሌለው ደረሰኝ ከቀረበ ተቀባይነት አይኖረውም፣
- ከህገ ወጥ ማለትም የአዘዋዋሪነት ወይም የአምራች ማህበር ውክልና ሳይኖረው ሲሸጥ ወይም ከእነዚህ አካላት ሲገዛ ወይም ሲያሻሽጥ ከተገኘ በህገ ወጥ ግብይት ምክንያት በተረፈ ምርት አይመዘገብለትም፣

5. ይህ የተረፈ ምርት ዉዳቂ /rejection/ መመሪያ በአዋጅ ቁጥር678/2002 የተረፈ ምርት አንቀጽ መሰረት ለኦፓል ማዕድን በመመሪያነት ያገለግላል፡፡

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር
መዝገብ ቤት
RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum